# አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

# እስከማዕዜኑ

"አቤቱ፣ እኔ ስጮህ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?"



የአቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ አራት መጽሐፍት በአንድ ላይ

- በመከራ ጊዜ
- እስከማዕዜኑ
- ቅዱስ እንባ
- እርጋታ



ጭቁኖቹ የግብጽ ኮፕቲክ ክርስቲያኖችም "የአባቶች አባት"፣ "የእረኞች እረኛ" ይሏቸዋል። "በወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ ሐዋርያዊ መንበር የእስክንድርያ ጳጳስ፣ የመላው አፍሪካ ፓትሪያርክ፣ የአባቶች ሁሉ አባት፣ የእረኞች ሁሉ እረኛ፣ የቅዱስ ማርቆስ ተተኪ፣ አስራሶስተኛው ሐዋርያ፣ የቤተክርስቲያን ዳኛ፣ የክርስቶስ ኢየሱስ ተወዳጅ" የሚለው ደፋዊ የማዕረግ ስማቸው ግብጻውያን "ኒል" እንደሚሉት እንደ አባይ ወንዝ የረዘመ ቢሆንም ማንም እንደማይገባቸው አድርጎ አያስብም።

117ኛው እስክንድርያው ጳጳስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ በረኸኛ ናቸው። ደግሞም ከመቶ በላይ መጻሕፍትንና ጽሁፎችን ያበረከቱ የቀለም ቀንዲል ናቸው። ከመላው አለም ወደ ስድሳ የሚሆኑ ሽልማቶችና ማዕረጎች ተበርክተውላቸዋል። አናሳዎቹ የግብጽ ክርስቲያኖች መብታቸው ተከብሮ በፍቅርና በክብር እንዲኖሩ ብዙ ለፍተዋል፣ እስከ ቁም እስር የደረሰ ክርስቲያናዊ መከራንም በደስታ ተቀብለዋል። የድካማቸውን ያህል ባይሆንም በመጠኑ ተሳክቶላቸዋል። በዚህም ከግብጻውያን መሪዎች እስከ ግብጻውያን ሙስሊሞች ድረስ ከፍተኛ አክብሮትን አግኝተዋል። ስፍር ቁጥር በሌላቸው አስተምህሮቶቻቸው፣ በጽሁፎቻቸውና በመጽሐፍቶቻቸው መላው ዓለም ያውቃቸዋል።

"አራት ሰው ሞተ ደረሰ እና ጥሪ
ደራሲ፣ ሰባኪ፣ ጳጳስ እና መሪ
እንግዲህ መቃብር ደኅና አርገህ እፈስ
መጽሐፍ ተሸክሞ መጣልህ ጳጳስ
በግብጽ በካይሮ ጩኸት በረከተ
የዓለሙን አናውቅም አንድ የእግዜር ሰው ሞተ
ሞተዋል እንዳይሉ ጽፈው አገኟቸው
አልሞቱም እንዳይሉ ተኝተው አዩዋቸው
ምናሉ ቅብጦቹ ሰው ሲጠይቃቸው
ለወሬ አልተመቸም በችግር ላይ ናቸው"

ሙዘዓ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት የአቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊን ህልፈተ ሕይወት ተከትሎ የቋጠራቸው ስንኞች

ብጹዕ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

# እስከማዕዜኑ

"አቤቱ፣ እኔ ስጮህ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?"

ትርጉም፦ ራስ ሥዕለክርስቶስ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
© All Rights Reserved

© መብቱ ሙሉ በሙሉ የአሳታሚው ነው፡፡

የመጀመሪያ ዕትም 2014 ዓ.ም

ቡክ ላንድ አሳታሚና አከፋፋይ፡-

+251 -922-74-02-02

+251 -930-08-33-08

# እነሆ ስጦታ

ለ ____________________

አራት መጽሐፍትን በአንድ ላይ የያዘው ይህ የብጽዕ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ **እስከማዕዜኑ** መጽሐፍ እስከ መቼ ጌታዬ ሆይ? ብለህ/ሽ ለምትጠይቃቸው/ቂያቸው ጥያቄዎችና ችግሮች ሁሉ መልስ እንዲሆንና መከራውንም ማሸነፊያ መንገዶችን እንዲያሳይህ/ሽ በመመኘት ተበረከተ።



# ማውጫ

"ቀዳሚ ቃል" ........ 7

መጽሐፍ 1. **በመከራ ጊዜ**

ምዕራፍ አንድ

**ጌታ ሆይ እንዴት?** ........ 11

ምዕራፍ ሁለት

**የዳዊት ወቀሳ** ........ 14

ምዕራፍ ሦስት

**"የሌሎች ቅዱሳት ወቀሳ"** ........ 21

ምዕራፍ አራት

**ዳዊት እንደ ክርስቶስ ምሳሌ** ........ 62

መጽሐፍ 2. **እስከማዕዜኑ**

ምዕራፍ አንድ

**ወደ ፈተናም አታግባን!** ........ 77

ምዕራፍ ሁለት

**እንዳልወድቅ፣ እንዳልጥልም ወዮልኝ!** ........ 91

ምዕራፍ ሦስት

**መቼ አርፋለሁ?** ........ 97

ምዕራፍ አራት

**እስከመቼ እንጠብቅ?** ........ 107

## መጽሐፍ 3. **ቅዱስ እንባ**


ምዕራፍ አንድ

**የልቅሶ ዓይነቶች** ..................... 119

ምዕራፍ ሁለት

**እንባ በአገልግሎት ውስጥ** ..................... 134

ምዕራፍ ሶስት

**እንባዎች በቅዱሳን ሕይወት** ..................... 141

ምዕራፍ አራት

**የእንባዎች ምክንያቶች** ..................... 150

ምዕራፍ አምስት

**"እንባ አድርቅ"** ..................... 174


## መጽሐፍ 4. **እርጋታ**


ምዕራፍ አንድ

**የእርጋታ ውበት እና ማራኪነት** ..................... 199

ምዕራፍ ሁለት

**የመረጋጋት ዓይነቶች** ..................... 228

ምዕራፍ ሦስት

**የእርጋታ ማጣት መንስኤዎች** ..................... 252

ምዕራፍ አራት

**እርጋታን እንዴት ማግኘት እንችላለን?** ..................... 276

# "ቀዳሚ ቃል"

ፈጣሪ አምላክ ፈቅዶ በዳዊት መዝሙራት ላይ ጥልቅ ምልከታዎቼን በ1968 መጨረሻና 1969 በአስተምህሮቶቼ እንዳጋራ በቅዱስ ፍቃዱ እድል አግቼ ነበር። በሌሎች ዘመናትም እንዲሁ መንፈሳዊ እሳቤዎችን የመረመርኩበት አንዱ የመዝሙሩ ክፍል "አቤቱ፤ የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ! በኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ናቸው?" የሚል ሲሆን ወቅቱም ዕለተ አርብ ሚያዝያ 18/1968 (እ.ኤ.አ) በአፅባኪያ የሚገኘው ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ነበር።

ይህም ክፍል ከዘወትር ማለዳ ፀሎታት አንደኛው መዝሙር ነው። ከመዝሙራቱ ውስጥ ለእዝነ ልቦናችን ለማስታወስ የቀለለውን በመምረጥ ነው ከጥቅል ትምህርቶቼ አስቀድሞ ጥልቅ ምልከታ ለማድረግ የተነሳሁት።

ውድ አንባቢያን ሆይ፣ እነዚያን ትርጓሜዎችና ምልከታዎች በአነስተኛ መጽሐፍት ቀንብቤ ለማቅረብ ስነሳ አስቀድሞ በመዝሙር 19(20) ማለትም **"በመከራ ቀን እግዚአብሔር ይስማህ..."** (መዝ 20፥1) በሚለው ክፍል ትንታኔዎችን ለማሳተም በቅቻለሁ። ይኸውም የሶስት ሰዓት ፀሎት ቀዳማዊው መዝሙር ነው። በ11ኛው ጸሎተ ክፍል ላይም ሶስቱ የመዝሙራቱ ክፍል ላይ በመመርኮዝ አስተምህሮዎችን አሳትሜያለሁ።

ፈጣሪ አምላክ በሚቀጥሉት ስብስብ ስራዎቼ ላይም እንደሚረዳኝ ተስፋ አለኝ… በፀሎታችሁ አስቡኝ።

**አቡነ ሽኖዳ ሣልሳዊ**

**በመከራ ጊዜ** | **እስከማዕዜኑ** | **ቅዱስ እንባ** | **እርጋታ**












**የደስታ ቀናት እንደ ሰማይ ሲርቁ…**
**ክፉ ቀናት እንደ አጀብ ሲከቡን…**
**የተጠበቀው ቀርቶ የልተጠበቀው ሲሆን…**
**ሞት እንደ አማራጭ ሆኖ ሲቀርብ…**
**ውስጣዊ ሰላማችን ሲረበሽ…**
**እርጋታ ፈጽሞ ሲጠፋ….**

…ያን ጊዜ “ጌታ ሆይ እስከመቼ?” እንላለን፡፡ ደግሞም በልጅነት ሰቆቃ በአባቶቻችን እንደበት “እስከማዕዜኑ?” እንላለን፡፡ እንባችን እንደ መጠጥ፣ ህዘናችንም እንደ መብል ይሆንብናል፡፡ የቀናት ጠንሳሽ የሆነው አባታችን እግዚአብሔር ግን “ታገስ፣ የመጠበቅን ፍሬ ትበላለህ” ማለቱን ይቀጥላል፤ እኛም “አምላኬ ሆይ፣ እንዴት ልታገስ? እስከመቼስ ልጠብቅ?” እንላለን፡፡ ከዚያም ቃሉን ያስታውሰናል፣ የቀደሙ ቅዱሳኑን አብነት ይዘክርልናል፡፡

“እንደ ልጄ እንደ ዳዊት ቀና ሁን፣ እንደ ታላቁ ታጋሽ እንደ ኢዮብ ሁንልኝ፣ የቀጠርኩልህ ቀን ሲደርስ የመከራህን ቀናት አስረሳሃለሁ! እንደ ተወዳጁ ልጄ እንደ ወልደ ትንሳኤህ እስኪገለጥ እርጋታን ገንዘብህ አድርግ!” ይለናል፡፡ በቅዱስ ቃሉ ያባብለናል፡፡

የህማማት ቀናቶቻችን እንደ ግዮን ወንዝ የረዘሙ ሲመስሉ፣ የህዝባችን እፎይታ፣ የሀገራችን ሰላምና መረጋጋት እንደ ጌታችን መምጫ ቀን ሲርቁብን፣ ህይወት ከንቱ፣ መኖርም ምናምንቴ መስሎ ሲታይ… የምድረ በዳው መንከራተት ከነዓናችንን ሊያስረሳን ሲደርስ፣ መራርነት ተስፋችንን ሊያስጥለን ሲተጋ፣ የስጋ ድካም ከዘለዓለማዊው እጣ ፈንታችን ሊያናጥበን ሲል… ያን ጊዜ የታላላቅ አባቶች ምክር፣ የቅዱሳን ጥበብ፣ የታጋሾች ምስክርነት ያስፈልገናል፡፡

እነዚህ የብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ስብስብ ደቂቅ መጻሕፍት የተጻፉትም ለዚሁ ዓላማ ነው፡፡ በጥሞና እንብባችሁ ትጠቀሙ ዘንድ እነሆ ከብዙ ጥንቃቄ ጋር ወደ አማርኛ ተርጉመን አቀርበንላችኋል፡፡

መልካም ንባብ!!

BOOK LAND
ቡክ ላንድ
0922740202

EIDO ADVERT

ዋጋ - 254.00 ብር

Salem Printing Press